# « በሀገራችን ዘመናዊ የግብር/የታክስ ስርዓት ለመዘርጋት የግብር ከፋዮች መለያ ቁጥር በጣት አሻራቸው ተደግፎ ምዝገባ እየተካሄደ ነው፡፡»



**መስከረም 4/2002 ዓ.ም የክልሉ ከፍተኛ ባለስልጣናት ጣት አሻራ በሚሰጡበት ወቅት**

ዛሬ ዛሬ ሀገራት በራሳቸው ጥረት ብቻ የሚበለፅጉበት ዘመን አክትሟል፡፡ ዘመኑ ግሎባላይዜሽን ነውና የቴክኖሎጂ ሽግግር ከአንደኛው ክፍለ ዓለም ወደ ሌላኛውም ክፍለ ዓለም ለመሻገር ጊዜ አይፈጅበትም፡፡ የእውቀት እና የልምድ ማነስ ከድህነት/ከኢኮኖሚ እጥረት/ ጋር ተደምሮ ካልገደበው በስተቀር ለየትኛውም ዓይነት የመረጃ ልውውጥ አልያም የቴክኖሎጂ ሽግግር ዓለም አንድ መንደር እየሆነች መጥታለችና፡፡

የተጨማሪ እሴት ታክስ ትግበራ ለመጀመሪያ ጊዜ ስራ ላይ የዋለው በፈረንሳይ ሀገር ነበር፡፡ ይሁንና ስርዓቱ ገቢ የማመንጨት አቅሙ ከፍተኛ ከመሆኑም በላይ ዘመናዊ የግብር/የታክስ አስተዳደር ስርዓትን የሚከተል በመሆኑ ዛሬ በዓለማችን በርካታ ሀገሮች በስራ ላይ በማዋል ተጠቃሚ በመሆናቸው ሀገራችንም ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ ይህንኑ የታክስ ስርዓት መተግበር ጀምራለች፡፡

ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ እንደዚሁ በጣት አሻራ የተደገፈ የግብር ከፋዮች የንግድ ምዝገባ ተጀምሯል፡፡ ሁለቱም የሌሎች ሀገሮች ተሞክሮዎች መሆናቸው ስለሚያመሳስላቸው ለግንዛቤ ያህል ስለተጨማሪ እሴት ታክስ በመግቢያው አነሳን እንጂ የዚህ ፅሁፍ ዋና ዓላማ በቅርቡ በሀገራችን በመተግበር ላይ ስላለው በጣት አሻራ የተደገፈ የግብር ከፋዮች የንግድ ምዝገባ/Biometric Tax Payer Identification System/ ምንነትና ጠቀሜታው እንዲሁም በሀገራችን ጅምር የምዝገባ እንቅስቃሴውንና አጠቃላይ ፋይዳውን ለመዳሰስ ነው፡፡

እስካሁን ድረስ በሀገራችን የታክስ/የግብር ስርዓት ውስጥ የሚታየው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የድግግሞሽ /TIN Duplication/ ችግር ከዚህ ቀደምም አለም አቀፋዊ ችግር ሆኖ አልፏል፡፡ ሌሎች ሀገሮች ይህን ችግር ለመቅረፍ የቻሉት በጣት አሻራ ላይ የተመሰረተ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር አሰጣጥ

ስርዓትን ተግባራዊ በማድረግ በመሆኑ በእኛም ሀገር ይህንን ዘዴ ተግባራዊ ማድረግ ግድ ብሏል፡፡ ለመሆኑ በጣት አሻራ የግብር ከፋዮች ንግድ ምዝገባ ማለት ምንድን ነው? ጠቀሜታውስ እንዴት ይገለፃል?--

**የጣት አሻራ/Finger Print/ ማለት**:- የጣት ውስጣዊ ፈለግ ወይም ጭረት ማለት ነው፡፡ የአንድ ግለሰብ አሻራ የራሱ ብቻ የሆነና በምንም ሁኔታ ከማንኛውም ሌላ ሰው ጋር /መንታነትም ሳይቀር/ የማይመሳሰል ልዩ የስነ ተፈጥሮ መለያ ነው፡፡

የግብር ከፋዩን ንግድ ምዝገባ በጣት አሻራ የተደገፈ ማድረጉ መሰረታዊ ጠቀሜታው ደግሞ በሀገራችን ዘመናዊ የግብር/የታክስ ስርዓት በመዘርጋት ፈጣን፣ ቀልጣፋና የተሟላ የግብር መረጃ አያያዝ ስርዓትን የማደራጀት ተልዕኮ ያለው ነው፡፡

የግብር ከፋዩን ማንነት በማያሻማ ሁኔታ ለመለየትና ከ/TIN/ መለያ ቁጥር ምዝገባ ጋር ተያይዞ የተከሰተውን የመለያ ቁጥር ድግግሞሽ ችግር ለመፍታት እንዲሁም የታክስ ስወራ እና ማጭበርበር ጋር የሚከሰተውን የተወሳሰበ ችግር ለመቅረፍ የተዘየደ ዘመናዊ የታክስ ስርዓት መሳሪያ ነው፡፡ እንዲሁም በአሁኑ ወቅት ሀገሮች አሻራን ለግብር ከፋይ መለያነት በተጨማሪ ለፓስፖርት፣ ለቪዛ፣ ለማሕበራዊ ደህንነት፣ ለሰራተኛ ቁጥር፣ ለክሬዲት ካርድም ይጠቀሙበታል፡፡

በተለይ ግብር/ታክስ መክፈል የሚገባውን ግለሰብ ወይም ድርጅት የተሰማራበትን የስራ ዘርፍ፣ አድራሻ እና አጠቃላይ መረጃ በመለየት በወቅቱ ገቢያቸውን አስታውቀው የሚከፍሉና የማይከፍሉ ግብር ከፋዮችን ለመቆጣጠር ያስቻለ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ስርዓትን እየተከተለ የአገልግሎት አሰጣጥ የሚያፋጥን በመሆኑ በግብር/በታክስ አሰባሰቡ ስራ ላይ እመርታዊ ለውጥ ያመጣል ተብሎ መንግስት ከፍተኛ ትኩረት የሰጠው የዘመናዊ የታክስ ስርዓት አካል ነው፡፡

በመሆኑም ይህን አሰራር /Biometric Tax payer identification system/ ተግባራዊ ለማድረግ መንግስት ከፍተኛ በጀት መድቦ ለመጀመሪያ ጊዜ በሀገራችን ከሚገኙ ግብር ከፋዮች ውስጥ 1.6 ሚሊዮን ግብር ከፋዮች ላይ የሚተገበረው ፕሮጀክት«ኮፒ ከት» በተሰኘ ዓለም አቀፍ አማካሪ ድርጅት አማካኝነት ከግንቦት ወር 2001 ዓ.ም በአዲስ አበባ መስተዳደር ተጀምሮ በአሁኑ ወቅት በክልሎችም የጣት አሻራ ምዝገባው እየተካሄደ ይገኛል፡፡

በአዲስ አበባ መስተዳደር ከግንቦት 1 እስከ ህዳር 5 በተካሄደው የግብር ከፋዮች የጣት አሻራ የመቀበል ስራ ከ352 ሺህ በላይ ግብር ከፋዮች የጣት አሻራቸውን ስለመስጠታቸው የምዝገባ መረጃው ያመለክታል፡፡

በክልላችን/በደቡብ ክልል/ የጣት አሻራ ምዝገባው የተጀመረው መስከረም 4/2002 ዓ.ም ጀምሮ በሀዋሳ እና አርባምንጭ ከተሞች ቢሆንም በተከታታይ በወላይታ ዞን፣ በደራሼ ልዩ ወረዳ፣ በጌዲዮ ዞን፣ በሲዳማ ዞን፣ ከፋ ዞን፣ ሀዲያ፣ ስልጤ ዞን፣ ቡታጅራ፣ ደ/አሞ፣ ዲላ፣ በኮንሶ ልዩ ወረዳ፣ እየተካሄደ ይገኛል፡፡ ከመስከረም 4 እስከ ህዳር 30/2002 ዓ.ም ድረስ በክልላችን ከላይ በተጠቀሱት ከተሞች በተካሄደው የጣት አሻራ ምዝገባ ብቻ ከ90 ሺህ በላይ ግብር ከፋዮች መመዝገብ ተችሏል፡፡ ከዚህም ውስጥ 34,989 የሚደርሱት የግብር ከፋዮች የተመዘገቡት በሀዋሳ ከተማ በተለያዩ የጣት አሻራ መቀበያ ጣቢያዎች በተካሄደው ምዝገባ ነው፡፡

ይህ ዘመናዊ የግብር/የታክስ አሰባሰብ ስርዓት አካል የሆነው የጣት አሻራ ንግድ ምዝገባ በአግባቡ ተከናውኖ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሲደረግ በሀገር አቀፍ ደረጃ የግብር አሰባሰብ ስራው ላይ ተጨባጭ ለውጥ ያመጣል፡፡

የጣት አሻራ ፕሮጀክቱ በሀገራችን በከፍተኛ ሁኔታ የተንሰራፋውን የታክስ ስወራ እና ማጭበርበር ችግር በመቅረፍ ሀገራችን በግብር/ታክስ መልክ የምትሰበስበውን ገቢ በእጅጉ ከማሳደጉም በላይ ሀገራችንም እንደ ሌሎች ሀገሮች ከሀገሪቱ ከሚመነጨው አጠቃላይ ኢኮኖሚ ተመጣጣኝ የሆነ ግብር/ታክስ መሰብሰብ ወደምትችልበት ደረጃ የሚያሸጋግራት ድልድይ እንደሆነም ተገምቷል፡፡

አንድ ሀገር በሀገሩ ውስጥ ከሚመነጨው ኢኮኖሚ ውስጥ 25 በመቶ የሚደርስ ገቢ በግብር/ታክስ መልክ መሰብሰብ እንደሚገባ ዓለም አቀፍ ስታንዳርድ ሆኖ ተቀምጧል፡፡ ኬንያ 19 በመቶ፣ ጅቡቲ 20 በመቶ፣ ጋና 21 በመቶ፣ መሰብሰብ ሲችሉ እስካሁን በሀገራችን እየተሰበሰበ ያለው ግን ከ12 በመቶ ያልዘለለ ሲሆን በክልላችን ደግሞ 2 መቶ ብቻ በመሆኑ አፈፃፀሙ ከጎረቤት ሀገሮቻችን ጋር ሲነፃፀር እንኳን ከዚህም ዘርፍ ምን ያህል ገቢ እያጣን መሆኑን ፍንትው አድርጎ ያሳየናል፡፡

ይሁን እንጂ አሁን ዘመናዊ የግብር/የታክስ ስርዓት የመዘርጋት ስራ ተጀምሯል የዚህን ስራ ትግበራ ተከትሎ የገቢ አሰባሰባችንም አብሮ የሚያድግ በመሆኑ ባለፉት 6 ዓመታት ያስመዘገብነውን የኢኮኖሚ ዕድገት ቀጣይ እንዲሆን ከማገዝ አንፃር ያለው ፋይዳም ከፍተኛ ነው፡፡

እንግዲህ ይህን ዋነኛ «የልማት ቁልፍ» ከግብ ለማድረስ የሚመለከታቸው መንግስታዊ ተቋማት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የንግዱ ማሕበረሰብ እና ህብረተሰቡ ለስኬታማነቱ በሀገራዊ ፍቅርና ልማት ዙሪያ ብሔራዊ መግባባት በመፍጠር ለስኬታማነቱ መተጋገዝና መቀናጀት እንዳለባቸው የደቡብ ክልል ገቢዎች ባለስልጣን ያምናል፡፡

## ☞ ምዝገባው የሚመለከታቸው ግብር ከፋዮች:-

- የመንግስት ተቀጣሪ ሰራተኞች፣
- መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅት ተቀጣሪዎች፣
- የግል ተቋማት ተቀጣሪዎች፣
- የመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ቤት ተማሪዎች፣
- በንግድ ስራ የተሰማሩ ነጋዴዎች እና
- የቤት እና የዕቃ አከራዮች ናቸው፡፡

**ሀገራችንን አብረን እናልማ በማለት በፈቃደኝነት ግብር የሚከፍል ማሕበረሰብ ለመፍጠር በጋራ እንስራ!!**

# እናመሰግናለን፡፡